የተሰጠ መግለጫ

መስከረም 23 ቀን 2012ዓ/ም

## ለትምህርት ጥራት አገር በቀል የትምህርት ፖሊሲ ይዘጋጅ!!

የትምህርት ስርዓት ባለው ላይ እየተጨመረ የአለም አቀፍ የሳይንስና የቴክኖሎጂ እድገትን ተንተረሶ ከአገሪቱ የፖለቲካ፣ የኤኮኖሚና የማህበራዊ እድገት ጋር በማጣጣም ደረጃ በደረጃ የሚያደግና የሚለወጥ ነው እንጂ መንግስት በተለወጠ ቁጥር ለፖለቲካ ፍጆታ እንዲያገለግል ተደርጎ መዘጋጀት የለበትም። ያለመታደል ሆኖ ደርግ በንጉሱ ጊዜ የነበረውን የትምህርት ፖሊሲ ከስሩ በማፈራረስ ለራሱ ለፖለቲካ ማራመጃ እንዲውል አድርጎ አዘጋጀ፣ በተመሳሳይ የወያኔ/ ኢህአዴግ አገዛዝም እንደዚሁ የደርጉን አፈራርሶ ለስርዓቱ በሚያመች ሁኔታ ቀረጸ። በ1986ዓም (እኢአ)በዓለም ባንክና በዓለም የገንዘብ አበዳሪዎች እገዛ መዋቅር ማስተካኪያ በሚል አገር በቀል ያልሆነ የትምህርት ፖሊሲ ነድፎ በተግባር ላይ እንዲውል አደረገ።

የወያኔ /ኢህአዴግ ትውልድ ገዳይ የትምህርት ፖሊሲ - ሀገራዊ ራእይ የሌለው በመሆኑ ኢትዮጵያዊነት እንዲኮስስ ፣ የአገር አንድነት እንዲለላ የጎሳ ልዩነት በመፍጠር ወጣቱ ትውልድ በጎሳው እንዲደራጅ፣ ጎሰኝነት እንዲስፋፋ አድርጓል።አሁን ላለውና ለተፈጠረው የሕዝብ መፈናቀል የዚሁ የጎሰኝነት ውጤት ነው። ፖሊሲው ዓለም አቀፍ የዩኒስኮን መሰረታዊ የሰው ልጆች መብት ማለትም ህጻናት በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው መማር ሲገባቸው በሚኖሩበት አካባቢ በክልሉ ቋንቋ በግድ እንዲማሩ ተደረገ።በዚህም የተነሳ በብዙ አካባቢዎች ህጻናት እንዳይማሩ ከቤት እንዲውሉ ተደርጓል።ፖሊሲው ከትምህርት ስራ ይልቅ በሕዝብ መካከል ጥርጣሬና ጥላቻ በማንገስ ለወያኔ/ኢህአዴግ የጎሳ ፖለቲካ ማራመጃ ምቹ ሁኔታ ፈጥሯል።የሙያ ትምህርት ዘርፉም የተባለውን የሰለጠነ የሰው ኃይል ሆነ ምቹ የማስተማሪያ ቦታና መሳሪያ ሳይዘጋጅ ሕዝቡን ለማታለል የታቀደ ባዶ ጫጫታ እንደሆነ ከውጤቱ ማየት ተችሏል በተለይ በአንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች ተግባራዊ የሆነው አሁዳዊ (Self -Contained Teaching Method) የማስተማሪያ ዘዴ የመምህራንን ይሁንታ ያላገኘና መምህራን ያልተቀበሉት በመሆኑ በውጤቱም 4ኛ ክፍል የደረሰ አንድ ህጻን ማንበብና መጻፍ ያለመቻሉ የትምህርት ፖሊሲውን ውድቀት የሚያሳይ ነው። እንዲሁም የ2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች የፕላዝማ የትምህርት አሰጣጥ ከጥቅሙ ጉዳቱ ያመዘነ እንደሆነ በተግባር ተስተውሏል።

የስርዓተ ትምህርት ለውጥ ሳይደረግ የመርጃ መጻሕፍት ለውጥ በተደጋጋሚ ማድረግ እንደ መፍትሔ ተቆጥሯል፤ ባንድ የትምህርት ዘመን ላንድ ዓመት እንኳን ሳያገለግሉ በሌላ መጻሕፍት መተካት፣ የተዘጋጁትም ቢሆኑ በመምህራን አስተያየት ያልዳበሩ በመሆናቸው ከኪሳራ በስተቀር የፈየዱት የለም፤የት/ ሚኒስቴር ባወጣው ዘገባ ባንድ ወቅት ብቻ ለመጻሕፍት ህትመት 150 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር እንደወጣ ተገልጿል።

በ2011 ማገባደጃ ወር ላይ በ5 ዓመታት ውስጥ የሚጠናቀቅ በ2013ዓም ተግባራዊ የሚሆን ባለ70 ገጽ የትምህርት ፍኖተ ካርታ ማዘጋጀቱን የትምህርት ሚኒስቴር ገልጿል። ጥናቱ የተካሄደው ካምብሪጅ አሰስመንት(Cambridge Assessment) በሚባል የውጪ ድርጅት ፣ አጥኚዎቹም የውጪ አገር ዜጎች፣ የተኮረጃውም ከጋና፣ ከኬንያና ከደቡብ አፍሪካ የትምህርት ፖሊሲዎች እንደሆነ ተብራርቷል። ስለ ትምህርት ፍኖተ ካርታ ጥናትን በሚመለከት ከትምህርት ሚኒስቴር የተሰጠው ምክኒያት ከፖለቲካ ተጽዕኖ ነጻነትን ፍለጋ ነው የሚል ነው። እንደአገላለጹ ከሆነ ነጻነት ከዚህ የለም የሚል መልዕክት እንዳለው ማወቅ ይቻላል።ያለ ነጻነት የትምህርት ጥራት እንዴት ይታሰባል? ለጥናቱ መነሻ የሆነው ደግሞ 4ኛ ክፍል የደረሱ ህጻናት ማንበብና መጻፍ አለመቻላቸው፤ 10ኛ ክፍል የጨረሱ ተማሪዎች ምንም ዓይነት እውቀት ሳይገበዩ መጨረሳቸው ነው የሚል ነው።ይህን በተመለከተ የቀድሞው የኢትዮጳያ መምህራን ማህበር (ኢመማ) ገና ከጅምሩ የወያኔ የትምህርት ፖሊሲ ትውልድ ገዳይ እንደሆነ በተደጋጋሚ ለኢትዮጳያ ህዝብ ገልጿል። ነገር ግን ሰሚ አልተገኘም።



P.O.Box 16632 Saint Paul, MN 55116 • Tel.: 403-402-0334 • Email: eta1941@yahoo.com

*በ1986ዓም ተግባራዊ የሆነው የወያኔ/ ኢህአዴግ የትምህርት ፖሊሲ የታገዘው በዓለም ባንክና በዓለም የገንዘብ አበዳሪዎች ሲሆን የአሁኑ የትምህርት ፍኖተ ካርታ ደግሞ ከካምብሪጅ አሰስመንት ነው። ሁለቱም የባእድ አገር ድርጅቶች ናቸው።ትምህርትን በእጅ አዙር ለራሳቸው ጥቅም ማስጠበቂያ ማድረግ የሚፈልጉ የውጪ መንግስታት ወኪሎች ናቸው። ለአገራችንና ለሕዝባችን የሚጠቅም የተማረ ትውልድ እንዲፈጠር የማይፈልጉ ሀገሪቱን ሁልጊዜም የእነሱ ጥገኛ ለማድረግ የሚሰሩ ናቸው። ፤አሁኑም ፍኖተ ካርታ ከወትሮው ከ1986ቱ የተለያ አይደለም አልሸሹም ዞር አሉ ነው።አድሮ ቃሪያ እንዲሉ። ለውጡ ምኑ ላይ ነው?*

*የትምህርት ውድቀት የአገር ውድቀት ነው።የትምህርት ጉዳይ ባለቤቱ የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው።የትምህርት ዘርፍ የሚመለከታቸውን መምህራን፣ ተማሪዎች፣ ወላጆች፣ በማግለል የሚዘጋጅ የትምህርት ፖሊሲ ውጤታማ አይሆንም፤ ለአገርም አይጠቅምም። መምህራንን፣ ተማሪዎችን፣ ወላጆችን የትምህርት ባለሙያዎችን ያካተተ አገር በቀል የትምህርት ፖሊሲ እንዲዘጋጅ መምህራን፣ ተማሪዎች፣ ወላጆች፣ ሁሉም የኢትዩጵያ ህዝብ መታገል ይኖርበታል። ለዚህ ደግሞ መሰረቱ የዲሞክራሲ መብቶች የመጻፍ፣ ሀሳብን በነጻነት የመግለጽ፣ የመሰብሰብና የመደራጀት መብቶች በተግባር ላይ መዋል ይኖርባቸዋል።የመምህራን የአካዳሚክ ነጻነት መስፈን፣ የተማሪዎች የመመከርት ሸንጎ መመስረት መቻልና በትምህርት ጉዳይ ሀሳብ የመስጠት ሁኔታ መፍጠር ለትምህርት ጥራት ቅድመ ሁኔታ ከሆኑት ውስጥ ዋነኛዎቹ ናቸው። የመምህራን የደመወዝ ሁኔታ ሳይሸሻል፣ ምቹ የማስተማሪያ ሁኔታዎች ባልታዘጋጁበት የትምህርት ጥራት ከቶውኑ ማሰብ አይቻልም።*

*በመጨረሻ መምህራን መብቶቻቸውን ለማስከበር ተላጣፊውን ማህበር በማስወገድ ማህበራቸውን ኢመማን ከትምህርት ቤት መሰረታዊ ማህበር ጀምሮ እስከ አገር አቀፍ ድረስ ከአገዛዙም ሆነ ከማንኛውም የፖለቲክ ድርጅት ጣልቃ ገቢነት ነጻ በሆነ መንገድ መመስረት የወቅቱ ተግባር መሆኑን በስደት የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር አስተባባሪ ኮሚቴ ያሳስባል።*

*የመምህራን መብት ይከበር!!!*
*ተላጣፊ መምህራን ማህበርን ለማሰውገድ ትግሉ ተጠናክሮ ይቀጥል!!*
*ለአገር በቀል የትምህርት ፖሊሲ እውን መሆን- እንታገል!!*